# ኢሳትን በመደገፍ ኢትዮጵያን በመበታተን የድርሻዎ ይወጡ!

ቅምሻ:

"ኢሳት ገለልተኛ ሚድያ ነኝ የሚለው ከእምነቱ ተነስቶ እንጅ ለጊዚያዊ ጥቅም አለመሆኑን ገልጸ አላፊው አግዳሚው ለሚያናፍሰው አሉባልታ ኢሳት መልስ ለመስጠት ጊዜውም ፍላጎቱም የለውም። ጊዜው ተረት ተረት የምናወራበት ሳይሆን ታሪክ የምንሰራበት ነው ሲል ተናግሮአል።" በነገራችን ላይ ምንም ተናጋሪው እንዲሁ ይበሉ እንጂ በኢሳት ዙሪያ የሚጻፉ ጽሑፎች ከፈጠሩት ነውጽና ተጽእኖ የተነሳ በተቋሙ ሰራተኞች አከባቢ ሳይቀር ከፍተኛ የሆነ ልዩነት: ክፍተቶችና አለመግባባቶች ከዚህም የተነሳ ጽሑፎቹ ተከትለው የተካሄዱ ስብሰባዎችና ውጤቶቻቸው አቶ ፋሲል የኔ አለም በአደባባይ ይናገራሉ ብሎ የሚጠብቅ ሰው የለም። “ታሪክ የምንሰራበት ጊዜ ነው” ላሉት ነገር እውነት ነው ሕዝብን በአሉባልታ ወሬ በማደናገር ሀገርን የማፈራረስ ታሪክ ለመስራት ቆርጠው መነሳታቸውን የሚያመላክት ነው። ነገ መንገዱ ለራሳቸው የት ቆርጦ እንደሚጥላቸው አስቀድሞ ማየት ቢሳናቸውም። በተረፈ ግን የፕሮፖጋዳው ማእከል ዋና ተጠሪ አቶ ፋሲል የኔ አለም ተናገሩት የተባለውን ቃል በማስመልከት ግለጽና ቀለል ባለ አገላለጽ በአጭሩ እንደሚከተለው ላስቀምተውና ወደ ዋና ርዕሰ ጉዳዩ ልለፍ። አቶ ፋሲል የኔ አለም አሉት የተባለውን ቃል ለማድመጥ ሊንኩን ይጨቁኑ (http://ethsat.com/video/ tubepress_video=KXsXSViikC4&tubepress_page=1)

የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ዕለተ ህልፈታቸው በይፋ ከመነገሩ በፊት ኢሳት ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ሞተዋል" እያለ ሲያሚርት ወደ ኋላ አከባቢም ማስታወቂያ ሚኒስትሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአዲስ ዓመት ካሉበት እንደሚገለጡ ሲናገሩ ቅጥረኞቹ (የኢሳት ሰራተኞች ማለት ነው) የሚገቡበት አጥተው በሚያሳፍር መልኩ "አይ! ያልነው እንዲህና እንዲያ ነው ... አድማጮቻችን በእመቤተ ይሁንባችሁ ... " የማለት ያክል አፈር ከመላስ ምንም ያልቀራቸው የቀድሞ ቃላቸውን ሽምጥጥ አድርገው በመካድ ነገሩ ለማድበስበስ ቢሞክሩም ከዚያ በፊት ግን “መንግስት የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሁኔታ የመናገር ግዴታ አለበት” እያሉ ሲወተውቱ በኢትዮጵያ የማስታወቂያ ሚኒስተር የሆኑት ዋና ሹም እንዲሁም ምክትላቸው በሚገርም ሁኔታ አሁን ኢሳት ለአድማጮቹ እየሰጠው ያለው ቃል ነበር የተናገሩት። ለአሉባልታ ጊዜ እንደሌላቸው በመግለጽ።

በመሰረቱ ኢሳት የባልቴት ወሬ ከመልቀምና እንደ የሰፈር አሮጊት ተራ አሉባልታ ከመሸረብ አልፎ ራሱን ግልጽ ለማድረግ ጊዜ አጣሁ የሚለው እንዴት ባለ የማይታወቅ ስራ ቢጠመድ ነው? አይደለምም እንጅ ተቋሙ የሕዝብ ነኝ ሲል እንደሚለፍፈው ከሕዝብ ዘንድ ለሚነሳ ተደጋጋሚ ጥያቄስ ግልጽና ቀጥተኛ የሆነ ምላሽ የማይሰጥበት ምክንያት ምንድ ነው? ለመሆኑ ስሜ ጠፋ ሲል ለአንዲት መጣጥፍ አጸፌታ ምላሽ ለመስጠት እንቅልፍ ያጣና መሬት የጠበበችበት ግለሰብ ማን ቢሆን ነው? ከቶ ሌላ አቶ ፋሲል የኔ አለም የሚባሉ የኢሳት ቅጥረኛ ግለሰብ ይኖሩ ይሆን እንዴ? እንግዲያውስ ከእርስዎ የባሰ ጥዋት የተናገረው ማታ የማይደግመው የዞረበት ጨለምተኛ ሰው ይሁንታውን ይሰጦት እንደሆነ እንጅ ራስዎትን በመስተዋት እያዩ "አሉት" ተብሎ ራስዎ በበላይነት በሚያዙት ጣቢያ የተነገረው ቃል ደግመው ያደመጡት እንደሆነ "እኔ ይህን አላልኩም" ሳይሉ እንደማይቀሩ እርግጠኛ ነኝ። ለማንኛውም ለአድማጮቻቸው ያላቸውን ንቀት “ጊዜ የለንም” ሲሉ እውነታውን ለማዳፈን የሞከሩ አቶ ፋሲል የኔ ዓለም የተባሉ ግልሰብ ስሜ ጠፋ! አገር ይያዝልኝ ሲሉም ለአንዲት 3/4 ገጽ ለማትሞላ መጣጥፍ ያለውንና የሌለውን እቅማቸው አጠራቅመው የጻፉትን ያነበበ ሰው ጉድ! ሳይሎት አይቀርም። “የቃሊቲው ሚስጢር ገምጋሚ ሲገመገሙ (ከፋሲል የኔዓለም)” http://ethiopiazare.com/articles/opinion/2407-fassil-yenealem።

ሌላው ስለ ተቋሙ የተጻፉና የሚጻፉ ጽሑፎች በመሉ እንደሆኑ ያለ አንዳች መረጃ የተሰነዘሩ ተራ ሂሶችም አይደሉም። በነገራችን ላይ ኢሳት እነዚህ ጽሑፎች በማስመልከት መልስ ለመስጠት ካለበትም እውነተኛ ሆኖ መገኘት ስለሚጠበቅበት በራሱ ጊዜ ለመዋረድ ካልሆነ በስተቀር መልስ ለመስጠት አይሞክራትም። በተጨማሪም ኢሳት በድርጅቱ ለሚሰነዘሩ ጠንካራ ሂሶች መልስ መስጠት ያቃተው ጊዜ አጥቶ ሳይሆን እየተባለ ያለው እውነት የመቋቋም ስብእና ስሌለው ጭምር ነው። እስቲ አቶ ፋሲል የኔ አለም በመነፖል ጠፍግገው የያዙትን መድረክ ለአፍታም ብትሆን ለዜጎች (ለኢትዮጵያውያን) ክፍት ያድርጉትና በድርጅቱ አካሄድና አሰራር ጭብጥ ላይ የተመረኮዘ ቅሬታ ያለን ዜጎች ፊት ለፊት ድምጻችን እናሰማ ያኔ ሕዝብ ቁርጡን ያውቃል። ይህን ለማድረግ ማለትም ኢሳት ዜጎች በዜግነታቸው ተቀብሎ ለማወያየት ጊዜ ከሌለው ግን እውነትም አቶ ፋሲል የኔ አለም እንዳሉት ኢሳት ታሪክ እየሰራ ነው።

የጽሑፉ ዓላማ:

ከርእሱ በግልጽ ለመረዳት እንደሚቻለው ለማስተላለፍ የተፈለገው ቁምነገር በየትኛውም መንገድ በብዙም በጥቂቱም ኢሳትን መደጎምና መርዳት ማለት የጥቂት ግለሰቦች ጎጀ ከማሞቅና ኪስ ከማሳበጥ ባለፈ በገዛ ሀገርህንና ሕዝብን እሳት ማንደድ: መገነጣጠልና መለያየትን እንዲሁም ሉዓላዊት በሆነችው ሀገረ ኢትዮጵያ በአንድነትዋ ላይ በአፍራሽ ተልእኮ ላይ መሰማራት ማለት እንደሆነ ለማሳወቅ ተጻፈ።

ሐተታ፡

የጽሑፉ ጭብጥ የጽሑፉ ዓላማ በሚያስተዋውቀው ክፍል ለማስፈር እንደተሞከረ ይህ ኢሳት በመባል የሚታወቀው የትጥቅ ትግል አራማጅ ሃይሎች ጎሳን ያማከለ እምነታቸው የሚገልጹበትና የሚያንጸባሩቁበት የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ማእከል የሆነው የሳይበር ሬድዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ ጉልህ ስህተቶቹን በማስተካከል ሀገርንና ሕዝብን የሚጠቅም ስራ ከመስራት ይልቅ ከእለት ወደ እለት እየሄደበት ያለው ትውልድን የሚያቀጭጭና የነገ ተስፋም የሚያጨልም ሀገር አስከፊ ወደ ሆነ የትርምስ ዓውድማ የሚከትና ቁልቁልም የሚደፋ ጠማማና የወረደ አካሄዱ ዓይኑን ከፍቶ ማየት ለተቻለው ዜጋ ሁሉ ግልጽ እየሆነ ለመምጣጡ ቅንጣት ታክል አልጠራጠርም።

ኢሳትና ታቦተ ቁልቢ ገብርኤል ለተቀላቀለባቸው ለአንዳንድ የኢሳት ደጋፊዎች እጅግ ቀላል የሆነ ጥያቄ በማንሳት ሐተታዬ ልጀምር። ነጻ፡ ገለልተኛ፡ ፍትሐዊና አማራጭ የመረጃ ምንጭ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማቅረብ ነው። የሚል መልስ እንደማይሰጡኝ እርግጠኛ ነኝ። ነጻ፡ ገለልተኛ፡ ፍትሐዊና አማራጭ የመረጃ ምንጭ እንዳልሆነ ኢሳት ራሱም ያውቃልና። ያም ሆነ ይህ ደጋፊ ሆይ! ለመሆኑ ገንዘብዎን ለኢሳት ሲሰጡ ከኢሳት ምን አገኛለው ብለው አስበው ነው? ኢሳትን በገንዘብዎ የሚደግፉ ስለ ትግራይና የትግራይ ተወላጆች የፈጠራ ወሬ ለመስማት ከሆነ ለኢሳት የሚሰጡትን ገንዘብ ትግራይ ድረስ በመሄድ ለምን የክልሉን አጠቃላይ እንቅስቃሴና የትግራይ ሕዝብ የሚገኝበት የኑሮ ሁኔታ በዓይንዎ አይተው ማመን እንደሚችሉ አላሰቡበትም? በስማ በለው በገዛ ወገንህ ላይ ጥርስን ከመንከስ ይልቅ (ለዛውም ገንዘቦትን ከፍለው)። ኢሳት ወደ ትግራይ ክልል ለመሄድ ልዩ የይለፍ መታወቂያ (ፓስፖርት) መያዝ አለቦት ብሎ አክሎ ካልዋሾትና ካላስፈራራዎት በስተቀርም ይህን ያክል ያሳሰቦትና እንቅልፍም የነሳዎት እውነት የኢትዮጵያ ጉዳይ ከሆነ ቀላሉ መንገድ ትግራይ ድረስ በመሄድ መሬት ላይ ያለውን ሐቅ ቢያረጋግጡ አይሻልም ወይ? ሞኝነት ይመስላል አይደል? እንግዲያውስ አገር ከመበተንና የዜጎች ደም ደመ ከልብ ከማድረግ ከመነሻው የሀገር ጉዳይ ቅናት የበላን ኢትዮጵያውያን ያደረግነው ይህንኑ ነው።

በተረፈ ከኢሳት ጎን የመሰለፍዎ ጉዳይ/ገንዘብዎን የሚሰጡት ምክንያት የኢሳት/የግንቦት 7 ራእይና አጀንዳ በመጋራትና በመደገፍ ከሆነ ግን ተጠቃሾቹ ነጻ ያልወጡ "ነጻ አውጪዎቹም" ሆኑ ያልተፈቱ የቁራ መልእክተኞች ለዓይን ማየት የማይፈልጉት ሕዝብ ከመዝገብ ተፍቆ: ለዘመናት አንድ ሆና የኖረችው ኢትዮጵያም ተበጣጥሳና ተበታትና ለመየት እስከ ሆነ ድረስ ጭኾቱና ጭፈራው እምባዛም ሳይደንቀን ነው። እንዲህ ያለ ነገር ደግሞ "አይደንቀንም!" ብቻ ተብሎ በቸልታ የሚታለፍ ሳይሆን የኢትዮጵያ አንድነት ጠብቆ የማስጠበቅ ድርሻ የዜጎች ሁሉ ግዴታ እንደመሆኑ መጠን ዜጎች በመላ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው አንድነትና ሰላም እስከ ደም ጠብታ ድረስ በመታመን ለሀገራችንና ለሕዝባችን ያለንን ፍቅር በተግባር እናሳይ ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን ለማስተላለፍ እወዳለሁ።

ይህ የምልበት ምክንያትም አይደለም ሰው እግዚአብሔርም ቢሆን ልጅ እንጅ የልጅ ልጅ እንደሌላው መጻህፍት ስለ አወሱልኝ ነው። እያንዳንዱ ትውልድ በዘመኑ ለሚሆን ነገር ሁሉ ድርሻውን የመወጣትና ሃላፊነት የመውሰድ ግዴታ አለበት። ይህ ሊሆንበት የቻለም ከጸሐይ በታች በነበር የሚቀጥል አንዳች ነገር አለመኖሩ ነው። ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ትናንት ስለነበረች፡ እንዲሁም ዛሬ ስላለች ብቻ ነገም ትኖራለች ብሎ ማመን ሲበዛ የዋህነት ነው። እንደ ዜጎች በጋራ ማድረግ የሚገባንና የሚጠበቅብን ከማድረግ ራሳችን የቆጠብን እንደሆነ አይደለም ሀገር ራስህን ማጣትም አለ። "ኢትዮጵያ ለዘልአለም ትኑር!" ብሎ ነገር እንደሆነም ከመልካም ምኞትና ግድግዳ ላይ የሚለጠፈው ነፋስ በነፈሰ ቁጥር መልኩ የሚጠፋ መፎክር ከመሆን አልፎ በምንም ዓይነት ተአምር ሌላ ሊሆን አይችልም። አገር እንደሆነች በመስዋእትነት በታጀበ በመልካም ስራ እንጅ በአፈ ታሪክና በመፎክር አትቆምም። ቅዱስ ሚካኤል ወይንም ደግሞ ቅዱስ ገብርኤል እንደሆኑም ከዙፋናቸው ወርደው ሀገርህን አይጠብቁልህም።

ጎበዝ! ኢትዮጵያ የምትባል በደርቅ መሬት የምትገኝ ሀገር እንጅ ኢትዮጵያ የምትባል በሰማይና በመሬት መካከል የምትገኝ እሳት የማይበላት: ወንዝ የማይሸረሽራት መለኮታዊ/ምትሃታዊ ሀገረ መላእክት አይደለችም። ሀገራችን በማለት የምንጠራት ኢትዮጵያ እግዚአብሔር ለብቻዋ በእጁ ጠፍጥፎ የሰራት ሀገርም አይደለችም። ኢትዮጵያ፡ እንደ ማናቸውም አሜሪካም ሆነች ዩጎዝላቪያ የሚባሉ

አገሮች የነበረችበትና ያለችበት በሳይንሳዊ ስመ አጠራርዋ "ምድር" ተብላ በምትታወቅ ፕላኔት የምትገኝ ሀገር ናት። ስለሆነም የሀገራችን እጣ ፈንታም እንደሆነ ከሁለቱ አንዱ ጽዋ የመጎንጨትዋ ነገር ሊያጠያይቀን አይገባም። ወይ ብዙ ሳለች አንድ እንደሆነች ትቀጥላለች ካልሆነ ደግሞ አንድ የነበረችው አገር ኢሳትን በመደጎምና በመደገፍ እንደ ቅርጫት ስጋ ተበጣጥሳ ነበረት ሀገር እንተ ትትበሃል ኢትዮጵያ እየተባለ በግእዝ በእዝልና በአራራይ ይዘፈንላታል። ደግሞ ለዘፈን!!

ውድ አንባቢ ሆይ! ለመሆኑ ሰው በገዛ ሰዉ/ወገኑ ለመጉዳት እንዴት ገንዘቡን ይሰጣል? አገሬን እወዳለሁ የሚል ዜጋ በምን ሂሳብ ነው ሀገሩን ለመበታተን ከተነሱ ልሂቃን አብሮ የሚሰራው? ዜጎች ለሀገራቸው ያላቸው ፍቅር የሚገልጹት በገዛ ሀገራቸው በማውደምና በማፈራረስ የሆነውስ ከመቼ ወዲህ ነው? ኧረ ለመሆኑ ዘመን በተቆጠረ ቁጥር፡ ምድር ሰፊ ሳለች እንደ መንደር እየጠበበች በመጣችበት፡ የሰው ልጅ በየትኛውም አቅጣጫ ከምን ጊዜ በላይ ፈጣን እድገትና ለውጥ በሚያሳይበት ሰዓት ኢትዮጵያውያን ከሌላው ዓለም ተለይተን እንደ ግመል ሽንት ወደኋላ የምንጎተትበት ምክንያት ምንድ ነው? ይህ አስከፊ ሁኔታችን ሳያስለቅሰን ቀርቶ ለሞተ ሰው ጨጉራችን በመጨት ፊታችንም በመቧጨር ብናጎራ ውለን ብናጎራ ብናድር ምን ዋጋ አለው?

ተው ያገሬ ሰው! ከሆነ በኋላ ለቅሶ፡ ዋይታና እሪታ ለማንም አይበጅም። መንፈስ ነው ሲባል ሲነገርለት የነበረው ተመናፍሶ ከቀረው ጭንጋፍ ትምህርት የማንወስደውስ ምን ይሉት አዚም በላያችን ላይ ቢሰለጥን ነው? ኢሳት እንደሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቅም አጀንዳ ቢኖረው ኖሮ ያለ መሳሳት ባለኝ ሁሉ በገንዘቤም በእውቀቴም የድርሻዬን ለመወጣት ማንም አይቀድመኝም ነበር። ዳሩ ግን ኢሳት ሀገርን ለማልማት ሳይሆን ሀገርንና ትውልድን ለመበተን የተሰለፈው ሃይል ድምጽ ማጉልያ ሆኖ በመገኘቱ እኔም ታጥቄበታለሁ። እናማ የሀገሬ ሰው ሆይ!

- አገሩን የሚወድ ዜጋ ምኞቱን ይከለክላል እንጅ ፈቃዱን አይከተልም፡
- አገሩን የሚወድ ግለሰብ አመጽን አጥብቆ ይቃወማል እንጅ ከአመጽ ጋር ሕብረት አይፈጥርም:
- ሕዝቡን የሚውድ ማህበረሰብ ወገኑን አደጋ ላይ የሚጥሉ ማኛቸው የጥቃት አይነቶች በንቃት እየተከታተለ ሕዝቡን ይታደጋል እንጅ ከጸረ- ሕዝብ ሃይሎች ጋር ተሰልፎ ተመልሶ የሕዝቡን ስጋ አይበላም! በማለት ስጽፍሎት ሳያውቁ በስህተት እያወቁም በድፍረት ኢሳትን በመደገፍ የተያያዙት ኢትዮጵያን የመበተን ድርጊት ቆም ብለው ያስቡበት ዘንድ ነው። ኢትዮጵያን የመበታተንና ሕዝቦችዋንም የማለያየት ሕልምና ራዕይ ካሎት ግን ኢሳትን በመደገፍ ህልሞትና ራዕዮትን እውን ያድርጉ። ኢሳትን በመደገፍ ኢትዮጵያን በመበታተን የድርሻዎ ይወጡ! ኢትዮጵያን የማፈራረስ ሰይጣናዊ ድርጊት የኢሳት ዋነኛ ተልእኮ ነው! አለሁ የሚለው፡ የቆመውም ለዚህ ነውና። ሀገር ለመበተን!!

ሀገርንና ማንነትህን መጠበቅ ህልምን የመፍታት ያክል ቀላል አይሆንም!

ዲ/ን ሙሉጌታ ወልደገብርኤል
E-mail- yetdgnayalehe@gmail.com
United States of America
Feb. 28, 2013